Jan 9, 2006

# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ለለውጥ የቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ሚና በቀውጢ ጊዜ
## መሽጋሸግ፥ መሰባሰብ!

ሸንፈት ከነአስከፊ መዘዙ በኅብረተሰባችን ላይ እንዳይወርድ የምንፈልግ አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች ሁሉ ማንኛውንም የትግል ስትራቴጂ ለመቀየስ ከምንም በፊት ዛሬ በአገራችን የተከሰተው የፖለቲካ ቀውስ ዋና ገጽታ በሁለት ኃይሎች መኻከል ያለ የአጀንዳና የአካሄድ ልዩነት የፈጠረው ፍጥጫ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

***የመጀመሪያው*** የአጀንዳ ልዩነት የወለደው ፍጥጫ ነው፡፡ በአንድ በኩል **"ድምፄ ይከበር"** በሚል ዴሞክራሲያዊ ዓላማ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ የሚደግፈው አጀንዳ አለ፡፡ በሌላ በኩል የሕዝብ ድምፅ ሰርቀው፥ የዴሞክራሲውን ሂደት ቀልብሰው ሥልጣን ላይ ለመቆናጠጥ ከምንም ዓይነት ግፍና የጭካኔ ድርጊት እንደማይመለሱ በማስመስከር ላይ ያሉ ጥቂት የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችና ካድሬዎቻቸው አሉ፡፡

**ሁለተኛው** የፍጥጫ ምንጭ የትግሉ "ባለቤትነት" ጉዳይ የሚወልደው ልዩነት ነው፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ይኸ ትግል ከማንምና ከሁሉም በፊት የእኛ የራሳችን ጉዳይ ነው በማለት "ታገሉልን" ማለት ሳይወጣቸው "ምሩን፥ አቅጣጫ ስጡን፥ አታግሉን፥ እንታገል፥ እንሰዋ" እያሉ ድምፃቸውን ከፍ፥ እራሳቸውን ቀና አድርገው በመጮህ ላይ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቡን የትግል ተሳትፎ ወሳኝነት ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ከዚህ ይልቅ ትግሉን በተቻለ መጠን ከሕዝብ ተነጥለው ከሚንሳፈፉ ጥቂቶች ጋር "ድርድር" በሚሉ ፈሊጥ ዙሪያ ለማካሄድ የሚጥሩ ጥቂት የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በመነሳት እነዚህ ጥቂት ፀረ-ሕዝቦች ሰላማዊ ሰልፎችንም ሆነ የቤት መዋል አድማዎችን ጨምሮ ማንኛውንም ሕዝቡን በትግሉ ውስጥ ለማሳተፍ የሚጠቁም እርምጃ "አመፅና ሕገ-ወጥ ሴራ" የሚል አጉል ትርጉም እየሰጡ እራሳቸው በሕዝባችን ተጋድሎ ላይ የሽብር አመፅና ሕገ-ወጥ የግፍ ዘመቻ እያካሄዱ ናቸው፡፡

የተደራጁ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በተለይም ደግሞ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በዚህ ታሪካዊ የሁለት ኃይሎች ትንንቅ ወገን ለይተናል ካሉ በትግል አጀንዳቸውም ሆነ በአካሄዳቸው በእርግጥ የሕዝብ ወገን ሆነው መታየት አለባቸው፡፡ የዚህን ታጋይ ሕዝብና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ልጆቹን የሰዋበትን የ"ድምፄ ይከበር" አጀንዳ ወደ ጎን ትተው በሌላ አጀንዳ መንቀሳቀስ አይችሉም፥ አይገባቸውምም፡፡ ለዚህ የሕዝብ አጀንዳ ቆመናል ካሉ ደግሞ እራሳቸውን እንደ ዋና የትግሉ ተዋንያን፥ ወሳኙን የሕዝብ እንቅስቃሴ እንደ ተቀጥላና አልባሌ ጉዳይ ቆጥረው፥ በሕዝብ ትግል ያልታጀበ ድርድርን ወይም ደግሞ "ፓርላማዊ ትግልን" እንደዋና የትግል ስልት መውሰድ የለባቸውም፡፡ ይኸንን ካደረጉ ለሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ብቻ እንጂ ለነሱም፥ ለአገራችንም የማይበጅ እጅግ አደገኛ ሂደት ውስጥ እየገቡ መሆናቸውን መገንዘብ አለባቸው፡፡

ከተቃዋሚ ኃይሎች መኻከል የኅብረቱ የቀድሞ መሪዎች ከወዲሁ እዚህ ወጥመድ ውስጥ ገብተው የሕዝቡን ትግል ፓርላማዊ ተቃውሞ በሚል ፈሊጥ የመተካት አቋም ተከትለዋል፡፡ ከቅንጅቱ ከወዲሁ አንዳንድ ተመራጮች በዚህ ጎዳና ላይ የተሰማሩ ሲሆን አመራሩ ደግሞ በበኩሉ መሠረታዊውን የሕዝቡን " የድምፄ ይከበር" አጀንዳ የማያካትት ባለ ስምንት ነጥብ የመደራደሪያ አሳብ አቅርቦ ፓርላማ ለመግባት በነዚህ ነጥቦች ዙሪያ

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁ./Tel. 251-1530945 (Fax)

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ ቁ./Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

በአለም-አቀፉ ኅብረተሰብ አምባሳደሮች አማካይነት ከሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ጋር ለመደራደር መዘጋጀቱን ይፋ ካደረገ ውሎ አድሯል።

በኅብረቱ የቀድሞ መሪዎች ፓርላማ መግባት ግራ መጋባት የጀመረው የሕዝባችን ተጋድሎ አንዳንድ የቅንጅት መሪዎች በዚህ አጀንዳና በዚህ በድርድር የትግል ዘዴ ተመርኩዘው እነሱም ፖርላማ መግባት ከወሰኑ በሕዝቡ ሰፈር ትልቅ ግራ መጋባት ይፈጥራል። እኛ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች በዚህ ሳቢያ ለሚከተለው ቀውስ ከወዲሁ የመውጫ ስትራቴጂ ካላወጣን የግንቦት ዴሞክራሲያዊ ተጋድሎ ለአስከፊ ሽንፈት ሊጋለጥ ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት አለን። ይኸ የሚሆነው በቅንጅቱ አመራር ቀደም ሲል የቀረቡት ስምንት ቅድመ-ሁኔታዎች ቁም ነገር ሳይኖራቸው ቀርቶ አይደለም። አላቸው። የዚያኑ ያህል ደግሞ ችግርም እንዳላቸው መታወቅ አለበት። አሁንም የቅንጅቱ መሪዎች በእስር ላይ እያሉና መላ የኢትዮጵያ ሕዝብም ኅብረታችንም እነሱንና ሌሎች በግፍ የታሰሩ ዜጎቻችንን ለማስፈታት ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ላይ እያለን አንዳንዶች በቅንጅቱ ስም እነኝህን ነጥቦች መሠረት አድርገው ከኢሕአዴግ ጋር "ድርድር" የማድረግ ዓላማ እንዳላቸው በመከሰቱ ነጥቦቹን ዳግም ማየቱ አግባብ ሆኖ አግኝተነዋል።

***የመጀመሪያው*** ችግር የሚመነጨው ከስምንቱ ቅድመ-ሁኔታዎች መኻከል በድርድር ሊገኝ የሚችለው ነጥብ የፓርላማውን የአሠራር ደንብ ቀይሮ በአንድ ሦስተኛ ድምፅ አጀንዳ የማስያዝ መብት እንዲታወቅ ከሚለው ቅድመ-ሁኔታ ነው። ይኸ የኢሕአዴግን የስርቆት "አብላጫ" (ማጆሪቲ) ሥልጣን የሚያረጋግጥና በምንም ዓይነት የማይነካ በመሆኑ በድርድርም ስምምነት ላይ ሊደረስበትና በተግባርም ሊውል የሚችል ነጥብ ነው። ነገር ግን ተደጋግሞ እንደተባለውና የኅብረቱ የቀድሞ መሪዎች የነበሩት አካሄድ በግልጽ እንዳሳየው ዛሬ ባለው ሁኔታ ወደ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ፓርላማ መግባት ከተያዘው የዴሞክራሲያዊ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) እና የሕዝብ ድምፅ ይከበር ከሚል ተጋድሎ አንፃር ሲታይ ምንም ፋይዳና እርባና የሌለው እርምጃ ነው።

***ሁለተኛው*** ችግር ከነዚህ ከስምንቱ ቅድመ-ሁኔታዎች ለዴሞክራሲያዊው ትግል ፋይዳ ያላቸው ሲኖሩ እነዚህን ግን በሕዝባዊ ትግል እንጅ በድርድር ሊገኙ የሚችሉ አለመሆናቸው ነው። ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ የሆነ ዳኝነትን፥ የመገናኛ ብዙኀን መለቀቅን፥ የነፃ ምርጫ ቦርድ መቋቋምን፥ የፖሊሱና የሠራዊቱ ከአንድ ፓርቲ (ሕወሓት/ኢሕአዴግ) ቁጥጥር ውጭ መሆንን የሚመለከቱት ቅድመ-ሁኔታዎች ለአቶ መለስ አገዛዝ (ለሕወሓት/ኢሕአዴግ) የኀልውና ምሰሶዎች በመሆናቸው ከዴሞክራሲያዊ ሂደትና ግንባታ (ዴሞክራታይዜሽን) ተጋድሎ መፋፋም፥ መቀነባበር፥ መሳካትና ከድል በመለስ የሚታሰቡ አይደሉም።

***ሦስተኛው*** ችግር በነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች መኻከል ያለውን የርስ በርስ የመጠፋፋት ትስስር የሚፈጥር አጣብቂኝ ነው። ዛሬ ባለው ሁኔታ ተደራድሮ ፓርላማ መግባት የሕዝቡን ትግል ላይ ብዥታ የሚፈጥር፥ የተቃዋሚውን ጎራ የሚከፍል፥ ሕዝባችንን ይዘን ትግሉን እንገፋለን የሚሉ ዴሞክራቶችንንና አገር-ወዳዶችን "በአክራሪነትና በአመፀኛነት" አስፈርጆ ለአስከፊ ፀረ-ሕዝብ አፈና፥ እመቃና ለዓለም-አቀፍ ብቸኝነት የሚዳርግ በአጭሩ በሕዝባዊ ትግሉና በኢትዮጵያ ሕዝብ የግንቦት ድሎች ኪሳራ የሚካሄድ እርምጃ ነው። የቅንጅቱ መሪዎች በተያዘው ድርድር ገፍተው የፓርላማው አሠራር ደንብ ተቀይሮ አጀንዳ ለማስያዝ የሚያስችል ስምምነት ላይ ተደርሷል ብለውና ይኸንን ግንጥል ስምምነት እንደ "ድል" ቆጥረው ወደዚህ የሌቦች ዋሻ ፓርላማ እንገባለን ቢሉ ይኸንን እውነታ አይቀይረውም። በዚህ ከተሄደ የቅንጅቱ አመራር ያቀረባቸው ቁም ነገር ያላቸው የሌሎቹ ቅድመ-ሁኔታዎች እውነትነት የውሃ ሽታ ሆኖ የሚቀርበት አደጋ አለ ማለት ነው።

ይኸንን አደጋ ተገንዝበን ለትግል ቆርጠን ከተነሳን "አለን" ብለን የምንኮራበት ለአንድ ትውልድ ያልታየ ለዴሞክራሲ ተጋድሎ የሚያመች የኃይል ሚዛን እንዳለ በእርግጠኛነት

መናገር እንችላለን። ከሰባ ሰባት ሚሊዮን ሕዝባችን የማያወላዳ በጣም አብላጫው ክፍል ይኸ ምርጫ ተጭበርብሯል፥ ድምፄ ተሰርቋል፥ ድሌ ይከበርልኝ እያለ በሰላማዊ ትግል ለመግፋት ቁርጠኝነቱን አሳይቷል። በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ግንባር-ቀደም ዜጎች ደግሞ በያለበት በዚህ ሕዝብ ውስጥ ተተክለው ትግሉን ለመቀጠል እየተዋደቁና አይከፍሉ መስዋዕትነት እየከፈሉ ናቸው። ሌሎች በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ በውጭው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን "የሕዝቡ ድምፅ ይከበር" በሚል መፈክር እየተንቀሳቀሱ በዲፕሎማሲውና በፖለቲካው መስክ እንዲሁም በሃሳብ፥ በገንዘብና በጉልበት ለአገራችን ነፃነት የሚደረገውን ተጋድሎ ለማገዝ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መልክና ስፋት እየተዋደቁ ናቸው።
**ይኸ ሕዝባዊ ማዕበል እንዲቀጥል ቁርጠኛነቱ ካለ ከወዲሁ ፓርላማ በገቡት ላይ ሌሎች ቢደረቡ በኅብረተሰቡ ውስጥ ትንሽ ተጨማሪና ጊዜአዊ ግራ መጋባትን ሊፈጥር ይችላል። ነገር ግን የአምሳም፥ የመቶም፥ የመቶ አምሳም ዜጎች ከሕዝባቸው ብቻ ሳይሆን ከየአባሎቻቸው፥ በውጭም በውስጥም ከሚገኙ ደጋፊዎቻቸውና በሚሊዮን እየተቆጠሩ በሕዝብ ድምፅ ይከበር ከሚሉ ዜጎች ተነጥለው ፓርላማ መግባታቸው ይኸንን ተጨባጭ የኃይል ሚዛን በምንም መንገድ አይቀይረውም። የግንቦቱን ታሪካዊና ሕዝባዊ የተጋድሎ ምዕራፍ ላለመዝጋት የቆረጡ ታጋዮች ሊቀጥሉትና ከሕዝባቸው ጋር ድል አድርገውና የግንቦትን ድል አስመልሰው ኢትዮጵያችንን የሰላም፥ የዴሞክራሲ፥ የወንድማማችነትና የብልጽግና ምድር ከማድረግ የሚያግዳቸው ምንም ነገር ሊኖር አይችልም።**
ሆኖም ይኸንን አዲስና አስቸጋሪ የትግል ምዕራፍ ስንያያዝ እኛ የኢትዮጵያ አገር ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ለቀጣዩ ትግል የተወሰኑ የጋራ ግንዛቤዎች ጨብጠን በሚመጡት ሳምንታት ወዴት እንደምንሄድና ይኸንን ትግል ወዴት እንደምንወስደው ግልፅ አቋም ይዘን መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

የጋራ ግንዛቤን በተመለከተ አንድ ቁም-ነገር በማውሳት እንቆጠባለን። የሕዝቡን ተጋድሎ በፓርላማዊ "የሰከነ ትግል" የመተካት ሁኔታ ከተከሰተ ችግሩ በኅብረተሰቡ ግራ መጋባት ብቻ አያቆምም። የሕዝባችን ትግል ተቀነባብሮና ተፋፍሞ ካልቀጠለ በተበተነና አንገቱን በደፋ ኅብረተሰብ ላይ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ቀጣይ እርምጃ ምን እንደሆነ ለመገመት ችግር የለውም። በተለይ በግንቦቱ ተጋድሎ ሳቢያ በያለበት እየተንቀሳቀሱ ሕዝባችንን በግንባር ቀደምነት ሲያንቀሳቅሱ ኢሕአዴግ ካድሬዎች ዓይን እየገቡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ታጋዮች ላይ ያነጣጠረ የአፈና፥ የግድያ፥ የእስራት፥ ከሥራ የመባረር ውርጅብኙ ከአሁኑ ይበልጥ ተስፋፍቶ በሚሊዮኖች ልብ ብሩኅ ተስፋ ፈንጥቆ የነበረው የግንቦት ተጋድሎ ምዕራፍ በደምና በእንባ መልሶ ለረጅም ጊዜ የሚዘጋበት አደጋ ይፈጠራል። ላለፉት አሥራ አራት ዓመታት እየወደቀ እየተነሳ በበርካታ ዜጎች መስዋዕትነት የተገነባው ነፃ ፕሬስ እስካሁን ያለውም በዛ ተብሎ ደብዛው የሚጠፋበት ሁኔታ ይከሰታል። የሕዝቡ ብሶትና አንጀት ማረር የሚወልደው ግራ መጋባት ልክ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች እንደሚመኙት ሕዝብ ከሕዝብ፥ ሐይማኖት ከሐይማኖት፥ አካባቢ ከአካባቢ፥ አንድ የቋንቋ ቡድን ከሌላው የቋንቋ ቡድን፥ ወዘተ... የሚናከስበት ትርምስ ፈጥሮ ዴሞክራሲያዊ ሂደትን በተመለከተ አገራችን በየመስኩ ከድጡ ወደ ማጡ እየገባች የመከራዋ ዘመን ለአሥርም ለሃያም ዓመታት የሚሟዘዝበት አስከፊ ሁኔታ ይፈጠራል። ከዚህ ስንነሳና እንዲህ ዓይነቱ አስከፊ ኩኔት እውን ሆኖ ሕዝባችን ለዚህ አስከፊ ሰቆቃ እንዳይጋለጥ ከፈለግን በሚመጡት ሳምንታት የሚጠበቅብንን ሃላፊነት በተገቢ ለመወጣት እንችል ዘንድ ተግባሮቻችንን መሸጋሸግና መሰባሰብ በሚሉት ሁለት ቃላት ማጠቃለል ይቻላል።

***መጀመሪያ*** በግንቦት ድሎች ዙሪያ የኃይሎች መሸጋሸግ ያስፈልጋል። በእኛ ግምት በመጭው ጊዜ ዋናውና አንገብጋቢ የሚሆነው ጥያቄ የግንቦትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከሽንፈት አትርፎ በኅብረተሰቡ ዴሞክራሲን የማስፈን ጥያቄ ስለሚሆን ወገናዊ የሆኑ የድርጅት ፕሮግራሞችና ስሌቶች ምንም ቦታም ሆነ ትርጉም አይኖራቸው። **የተያዘው ትግል ድርጅቶች ሕዝብ ፊት ቀርበው የሚፋለሙበት የምርጫ ትግል አይደለም። ሕዝባችን ታግሎ፥ ተሰውቶና መርጦ ያገኘውን ድል የማስመለስም ትግል ብቻ አይደለም። በአገራችን**

የዴሞክራሲ ጭላንጭል ጠፍቶ የሽብር አገዛዝ እንዳይሰፍን የሚደረግ የመላው ኅብረተሰባችን የአልሞት ባይ ተጋዳይ ትግል ነው፡፡

በመሆኑም ተጋድሎው ከጥቂት የፖለቲካ መሪዎችም ሆነ ከፖለቲካ ድርጅቶች አልፎ መሄድ ያለበትና የሚሄድ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ተማሪዎች፥ ወጣቶች፥ ሴቶች፥ የሙያ ማኅበራት፥ ጋዜጠኞች፥ ምሁራን፥ የባህልና የልዩ ልዩ ጥቅም-አስከባሪ ስብስቦች፥ ወዘተ... ) ከፖለቲካ ኃይሎች እኩል ያገባናል ብለው የሚሳተፉበትም፥ የሚመሩትም ትግል መሆን ይኖርበታል፡፡

ስለዚህም ዛሬ በኢትዮጵያ ሽንፈትን አሻፈረን ብለው ትግሉን ለመቀጠል የሚፈልጉ ኃይሎች በሙሉ የድርጅት አባልነትና ደጋፊነት አጥር ሳይወስናቸው "ዜጎች ለግንቦት ድሎች" በሚል አንድ የጋራና ሕዝባዊ መፈክር ሥር ለመታገል መሽጋሸግ ይኖርባቸዋል፡፡

ሁለተኛ በዚህ ሕዝባዊ መፈክር ሥር የሚሽጋሸጉት ኃይሎች ለዚህ የጋራ ዓላማ የሚደረገውን ተጋድሎ ፈር ለማስያዝ በአንድ ሰፊና ሁሉን አቀፍ በሆነ "የቀውጢ ጊዜ አካል" ሥር መሰባሰብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይኽንን እውን ለማድረግ በቅንጅቱና በኅብረቱ ውስጥ የተካተቱ ሕዝባዊ ትግሉን ለመቀጠል የቆረጡ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች፥ የነዚህ ድርጅቶች የድጋፍ ኮሚቴዎች ተጠሪዎች፥ የሲቪኩ ማኅበረሰብ መሪዎችና ታጋዮች፥ እንዲሁም በያለበት "የሕዝቡ ድምፅ ይከበር" ብለው በመታገል ላይ ያሉ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ስብስቦች በአስቸኳይ ተገናኝተውና መክረው ላለንበት የቀውስ ወቅት የሚመጥን የጋራ ስትራቴጂ የሚነደፍበትንና ለዚህም አንድ የጋራ ትግል አካል የሚቋቋምበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይዋል ይደር የማይባል አገራዊ ግዴታ ነውና እነሆ ሁሉም ተግባራዊ መልስ እንዲሰጥ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

በጋራ ትግል ወደ ጋራ ድል!
የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ትግሉ መብቱን ያስከብራል!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ታኅሣስ ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም